# ዓመጽማ ኣይቀርም!

ከዓሣዬ

04/30/10

በትግሉ ሂደት ውሥጥ፣እኛ እሥከምናውቀው
የግንቦትን ዓመጽ፣ክዶ ያኮላሸው
ወሬ ኣሣመርኩ ብሎ፣በድንገት ሣያውቀው
እየተናነቀው የዓመጽ ቃል ቢያመልጠው
በኣድር ባዩ ጩኸት፣ዘረኞች ደንግጠው
ሚይዝ ሚጨብጡት፣መላቅጡን ኣጥተው
በኣመጽ ሊያወርዱን ነው ጺላጦሶች ብለው
የጦርነት ፈጣሪ፣ነፍሰገዳዮቹ፣በፍርሃት ተውጠው
ኡኡታ ኣሰሙ ኣሉ፣በዛቻ ደንብረው።

ዓመጽማ ኣይቀርም፣ይመጣል ገሥግሶ
በኣራቱም ማዕዘናት፣ሕዝቡ ተነሣሥቶ
የወያኔን መንደር፣ደርምሶ ኣፈራርሶ
የፋሺሥት፣ዘረኛን መቀበሪያ ምሶ
ዳግም ላይነሣ፣ኣፈሩን ኣልብሶ
በከሃዲዎች ሣይሆን!
በቁርጥ ቀን ልጆቹ፣ዘረኛን ገርሥሶ
የሃገር ልዕልናን፣ክብሯን ኣሥመልሶ
በሶሻል ዴሞክራሲ፣ሥርዓቷን ኣንጾ!።

ታድያኮ!
ያለ ምክንያት ኣይደለም፣ወያኔ መደንበሩ
ከሃዲም፣ካለ ሞያው፣የኣመጽ ቅብጥሩ፣
ሁሉም ገደል ኣፋፍ፣መሆናቸውን ጠርጥረው
በጣረ ሞት ሲቃ፣በፍርሃት ተንጠው
በጭቁኑ ሕዝባችን፣በዓመጽ ተሸቀንጥረው
በሰፈሩት ቁና፣እነሱም ተሰፍረው
ትግሉ ተቀጣጥሎ፣ባፍ ጢም ሊደፋቸው
መሆኑን ቢያውቁት ነው፣ጠራርጎ የሚያጠፋቸው!።

EthioLion.com